# በሶስተኛና አራተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍት የስርዓተጾታ ፍትሃዊነት ፍተሻ

**አራጋው ሺባባው ሞላ**[1]

**አጠቃሎ**

***ይህ ጥናት በሶስተኛና በአራተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍት የስርዓተጾታ ፍትሃዊነት ምን እንደሚመስሉ መመርመር ላይ ያተኮረ ነው። ለዚህም ሁለቱ መማሪያ መጻህፍት በዓላማ ተኮር ስልት ተመርጠዋል። መረጃዎችም በሰነድ ፍተሻ ስልት ተሰብስበዋል። የተሰበሰቡ መረጃዎም በካይ ካሬ፣ በድግግሞሽ ቆጠራ፣በሬሾና በመቶኛ ተተንትነዋል። ከተገኘው ትንተና እንደተስተዋለውም፣ ሴቶች በስም የቀረቡበት የድግግሞሽ መጠን*** *66(54.09%)* ***ሲሆን ወንዶች የቀረቡበት የድግግሞሽ መጠን ደግሞ*** *56(45.9%)* ***ነው። የካይ ካሬ ፍተሻ እንዳሳየውም*** *p>0.05* ***ሆኗል። የጉልህነት ውጤቱም*** *.157* ***ሆኗል። ይህም በሁለቱ ጾታዎች መካከል የጎላ ልዩነት እንደሌለ የሚያሳይ ነው። የሴት ወንድ የስም ድግግሞሽ ሬሾ/ጥምርታ/ ሲታይ ደግሞ*** *1.12* ***ሴት ለ****1* ***ወንድ ነው፡፡ ከዚህ አንጻርም በጾታ ድግግሞሽ የጎላ ልዩነት አልተስተዋለበትም። የሁለቱ ጾታዎች ማህበራዊ ሚና ሲታይ መጻህፍቱ ሴቶች ዋናዋና በሚባል ደረጃ በብዛት የቀረቡበት ሚና የለም። ከተሳተፉባቸው ሚናዎች መካከል ግን ሴቶችን መግረዝ፣ ዳቦ መግዛት፣ ዳቦ መሸጥ፣ ልጅ መንከባከብ፣ የህክምና ምክር መስጠት፣ መብት መጠየቅ፣ በሽተኛ መንከባከብ ይገኙበታል። ኳስ መጫዎት፣ በሽተኛ ተሸካሚ መሆን፣ ሩጫ ደጋፊ መሆን፣ ሳርቤት መክደን፣ፖሊስና ሹፌር ሆኖ መስራት ወንዶች በብዛት የተሳተፉባቸው ዋናዋና ሚናዎች ናቸው። ከዚህ አንጻር ሚና ላይ የፍትሃዊነት ችግር አለ ማለት ይቻላል፡፡ ውክልናን በተመለከተ ደግሞ በሁለቱም ጾታዎች ሴት ወይም ወንድ ሲባል ትዝ በሚል መንገድ የተስተዋሉ ውክልናዎች የሉም ማለት ይቻላል፡፡ ሳይደጋገሙ የቀረቡ ውክልናዎች ሲታዩ ግን ወንዶች በአንጻራዊነት በተሻሉ ነገሮች የተወከሉ ሲሆን ሴቶች ደግሞ ዝቅ ባሉ ነገሮች ተወክለው ቀርበዋል። ይህም ከውክልና አንጻር ክፍተት መኖሩን የሚያሳይ ነው። በመሆኑም ወደፊት የስርዓተትምህርት አዘጋጆች በሚያዘጋጁቸው መጻህፍት ጥንካሬዎቹን በማስቀጠል በድክመቶቹ በኩል ማሻሻያ ቢያደርጉ መልካም ነው።***

***ቁልፍ ቃላት፤ መማሪያ መጽሃፍ፣ ስርዓተ-ጾታ፣ ሚና፣ ውክልና***

## መግቢያ

**መማሪያ መጻህፍት ከስርዓተትምህርት ማስፈጸሚያ መሳሪያዎች በቀዳሚነት የሚጠቀሱ ናቸው። የቋንቋ መማሪያ መጻህፍት የተለያዩ ክሂሎችንና የዕውቀት ዘርፎችን ለማስተማር ወይም ለማለማመድ የሚያስችሉ ልዩልዩ ምንባቦችንና ተግባራትን የያዙ መሳሪያዎች ናቸው። አስፈላጊ የሆኑ አስተሳሰባዊ ወይም ቁሳዊ መረጃዎችን ለዜጎች ማድረስ የሚቻለው በእነዚሁ መሳሪያዎች ነው። ካላቸው የጎላ ሚና አንጻርም ‹‹የአንድ የትምህርት ፖሊሲ ልቦች›› ይሏቸዋል** (Carole፣ 2009)።

**መማሪያ መጻህፍት ህጻናትን የማስተማር ሚናቸው ከፍተኛ ነው። ማንኛውንም መረጃ ለማህበረሰቡ የማድረስ ብቃት ስላላቸው ከፍተኛ የመረጃ ምንጮች ናቸው። ምንም አይነት አጋዥ መጻህፍት በሌሉበት ቤት ውስጥ የመገኘት እድላቸው ሰፊ ነው። ለመምህራንም መሰረታዊ፣ አልፎ አልፎም ብቸኛ የመረጃ ምንጭ ወይም የማስተማሪያ መሳሪያ ሆነው ያገለግላሉ። በመጻህፍቱ የሚካተት ማንኛውም ነገር ህጻናት በሰፊው የሚጋለጡበት በአመለካከታቸው ላይ ተጽዕኖ ሊፈጥር የሚችል ሊሆን ይችላል። በመሆኑም በመጻህፍቱ መካተት ያለበት ነገር ሁሉ ተገቢ መሆን ይኖርበታል፡፡ በዚህም ህጻናት በዕለት ከዕለት የማንበብ ልምዳቸው በመጻህፍት የሚያገኟቸውን አስተሳሰቦች ይላበሳሉ** (Toci & Aliu፣ 2013፣ Akam፣ 2009**ና** Carole፣ 2009)፡፡ Toci & Aliu (2013)፣ Sumalatha (2004)**ን ጠቅሰው እንደሚያስረዱትም፣ መማሪያ መጻህፍት የህጻናትን የወደፊት ህይወት የሚመሩ መሳሪያዎች ናቸው። በመሆኑም በዝግጅት ጊዜ ሊተኮርባቸው ይገባል።**

**በመማሪያ መጻህፍት ዝግጅት ሂደት ሊተኮርባቸው ከሚገቡ የመጻህፍቱ ጉዳዮች መካከል ስርዓተጾታ አንዱ ነው። የስርዓተጾታን ምንነት በተመለከተ አንድ ወጥ ብያኔ አይስተዋልም። ለምሳሌ፣ አንዳንዶቹ ስርዓተጾታን በሴትና በወንድ መካከል ያለ ልዩነት፣ አንዳንዶቹ ደግሞ ከአካላዊ ባህሪ ጋር ያለ ልዩነት፣ አንዳንዶቹ ደግሞ ሴቶችን ከሃገር ዕድገት ጋር በማስተሳሰር ስርዓተጾታን ከእድገት ጋር ካለው ግንኙነት በማያያዝ ብያኔ ሲሰጡት ይስተዋላል።** Cranny-Francis, A. et al (2003) **ስርዓተጾታን በሁለት አቅጣጫ በመክፈል ‹‹የወንድና የሴት ልዩነት ነው›› ይሉታል፡፡** Hornby (1989) **ደግሞ ‹‹ስርዓተጾታ ማለት የጾታ ልዩነት ነው›› በማለት ብያኔ**

1 ጎንደር ዩኒቨርሲቲ ማህበራዊ ሳይንስና ስነሰብዕ ኮሌጅ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ- አማርኛ ትምህርት ክፍል

ይሰጡታል። Kevane (2004፣1) በበኩላቸው <<ለወንዶችና ለሴቶች የተሰጠ ባህላዊና ማህበራዊ የአወቃቀር ስርዓት ነው>> ብለው ይበይኑታል።

የስርዓተጾታ ጉዳይ አወዛጋቢነቱ እንደቀጠለ ቢሆንም በመላው ዓለም ግን በአሁኑ ሰዓት ትኩረት ያገኘ ጉዳይ ሆኗል። ተቋማዊ ሁኔታም ይዟል። በዩኒቨርሲቲዎችም የህብረተሰብ እድገትና የስነማህበረሰብ ጥናቶች ትኩረት ተሰጥቷቸው ይገኛሉ። ጾታ እንደአንድ የንድፈሃሳብ መስክም የተለያዩ ንድፈሃሳቦች የመነጩበት ሆኗል። ከንድፈሃሳቦቹም መካከል ሊበራል (liberal) አንዱ ነው። ይህ ንድፍሃሳብ የሴቶችን ነጻነት፣ ሴቶች ከወንዶች እኩል የትምህርት እድል እንዲያገኙ፣ ከወንዶች ጭቀና እንዲላቀቁ፣ በውሳኔ አሰጣጦች እንዲሳተፉ፣ ስራን በፍላጎታቸው እንዲመርጡ የሚሉ ሃሳቦችን በትኩረት ያነሳ ከ18ኛ ክፍለዘመን ጀምሮ የነበረ ቀደምት ንድፈሃሳብ ነው። ቀጥተኛ (radical) የሚለው ሁለተኛው ነው። ይህ ንድፈሃሳብ በጥራትም በብቃትም ሁሉም ጾታዎች እኩል የትምህርት እድል ያግኙ፣ ወንዶች ሴቶች ላይ ያላቸው የበላይነት እንዲስተካከልና ሴቶች በትምህርት የስልጣን እድል እንዲያገኙ ይታገላል። ማርክሲስት (Marxist) ደግሞ ሶስተኛው ነው። ይህ ንድፈሃሳብ ሴቶች ኋላቀር ከሆኑ የቤት ውስጥ ተግባራት ወጥተው ሀገራዊ ወይም ብሄራዊ በሆኑ ተግባራት እንዲሳተፉና ሁለቱም ጾታዎች እኩል የገንዘብ ድጋፍ እንደሚያስፈልጋቸው ታግለዋል። ሴቶች በየደረጃው/መደቡ ለበታችነትና ለጭቀና የተጋለጡበትን ምክንያት አጠንክረው ያነሳሉ። ማህበራዊያን (socialist) የሚለው ደግሞ አራተኛው ነው። ይህ ንድፈሃሳብ ከቀጥተኛና ማርክሲስት ንድፈሃሳብ የተነሳ ነው። ይህ ንድፈሃሳብ ሴቶች በማህበራዊም ሆነ በመንግስታዊ መዋቅሮች ከወንዶች የበታች እንዳይሆኑ የሚከራከር ነው። ለሴቶች የበታችነት ቁልፉ ትምህርት መሆኑን ያሳያሉ። እነዚህ ንድፈሃሳቦች ከስርዓተጾታ አንጻር የስራ ክፍፍል ምክንያቶች፣ የቤት ውስጥ የስራ ጫናና ተግዳሮቶች፣ ሴቶች እንዴት ሃላፊነትን ሊወስዱ ይችላሉ? ስለሚሉ ጉዳዮች ትንታኔዎችን ይሰጣሉ። ንድፈሃሳቦቹ የየራሳቸው መነሻ ጉዳይ ቢኖራቸውም የመጨረሻ ግባቸው ግን የጾታ እኩልነትን አስፈላጊነት የሚያሳዩ ናቸው። ለእኩልነቱም የማህበረሰባዊያን አንስታይ ንድፈሃሳብ አቀንቃኞች እንደገለጹት ሴቶች በማህበራዊም ሆነ በመንግስታዊ መዋቅሮች ከወንዶች የበታች እንዳይሆኑ ቁልፉ ትምህርት መሆኑን ያሳያሉ (Akam ፣ 2009፣ Cornwall, Harrison & Whitehead፣ 2007)።

መማሪያ መጻህፍት ከስርዓተጾታ ፍትሃዊነት አንጻር ምን እንደሚመስል የተለያዩ ጥናቶች በአገር ውጭና በአገር ውስጥ ተካሂደዋል። ለምሳሌ፡- በቻይና ሆንግ ኮንግ Jackie (2002) በቀደምትና በዘመናዊ የመማሪያ መጻህፍት ላይ ከስርዓተጾታ አንጻር ግምገማዊ ጥናት አካሂደዋል፡፡ በቀደምት መማሪያ መጻህፍት የወንዶችና የሴቶች የመከሰት ድግግሞሽ ሲታይ በተከታታይ 55.2% እና 44.8% ሲሆን በዘመናዊ መጻህፍትም እንዲሁ በተከታታይ 51.5% እና 48.5% ሆኖ ተስተውሏል። ይህ የውጤት መቀራረብም በመማሪያ መጻህፍት የስርዓተጾታን አመለካከት ለማስተካከል ትኩረት መሰጠቱንና ባግባቡ መታየቱን የሚያመለክት ነው፡፡ Taylor (2003) በአሜሪካ ባጠኑት ጥናት የተገኘው ውጤት እንደሚያመለክተውም መማሪያ መጽሃፉ ትንሽ ወንዶችን የሚያሞግስ፣ ሴቶችን የሚያኮስስ ነበር፡፡ ወንዶች እንደጠንካራ፣ የበርካታ ራዕይ ባለቤት ሆነው፣ ሴቶች ደግሞ የቤት ንጽህና የሚጠብቁና ምግብ የሚያበስሉ ሆነው ቀርበውበታል።

Candida & et al (1999)፣ በጥናታቸው የወንዶችንና የሴቶችን ባህላዊ መገለጫዎች ሲገልጹ፣ ሴቶች በወንዶች ስር ያሉ፣ ጥገኛ፣ ሰነፍ፣ ስሜታዊ፣ ተቀባይ፣ ደካማ፣ ፍዝ፣ ተደጋፊ፣ የወሲብ አገልግሎት ሰጭ፣ ለነገሮች ቅርብ፣ በአካላዊ ሁኔታ ሳቢ እንደሆኑ ሲጠቁሙ፣ ወንዶች ደግሞ የበላይ፣ ራሱን የቻለ፣ ጎበዝ፣ ምክንያታዊ፣ ሰጭ፣ ጠንካራ፣ ንቁ፣ ተወዳዳሪ፣ የወሲብ የበላይ፣ ቶሎ የማይደንቃቸው በማለት ነበር።

Wondifraw (2017) ከ5-8ኛ ክፍል ያሉ የማህበራዊ ሳይንስ መጻህፍት ባህለብዙህነትን ተደራሽ የማድረጋቸውን ሁኔታ አጥንተዋል። የተገኘው ውጤት የኢትዮጵያ የመጀመሪያ ደረጃ ሁለተኛ እርከን ማህበራዊ ሳይንስ መጻህፍት ባህለብዙህነትን አንጸባርቀዋል። ነገርግን ሴቶች በተወሰኑ መገለጫዎች ዝቅተኛ ውክልና (under represented) ይዘው ተስተውሏል። አጥኝው በቀጣይ መማሪያ መጻህፍት ሲዘጋጁ የጾታ እኩልነት ችግር ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባ ጠቁመዋል።

በኢትዮጵያ የተካሄደው ጥናት በማህበራዊ ሳይንስ መጻህፍት በባህለብዝሃነት ላይ ያተኮረ ነበር። በቻይና የተከናወነው በወንዶችና በሴቶች ድግግሞሽ መከሰት ላይ ማተኮሩ፣ በአሜሪካ የተካሄደው ደግሞ ውክልና ላይ ማተኮሩ ከዚህ ጥናት ልዩ ያደርጋቸዋል። ይህ ጥናት ድግግሞሽን፣ ውክልናን፣ ሚናን እንዲሁም ተያያዥ ችግሮችንና መፍትሄዎችን ከአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍት አንጻር የሚመለከት መሆኑ በዓላማ፣ በጊዜና በተጠኝ ልዩ ያደርገዋል።

በኢትዮጵያ ደረጃ የስርዓተጾታ አድሎን በተመለከተ በተለያዩ ማህበራዊ አውዶች ችግሩ እንዳለ ድርሳናት ይጠቅሳሉ። በመሆኑም አገሪቱ በሚሊኒየም የዕድገት ግብ ዕቅዷ የጾታ እኩልነት ችግሮችን በአንደኛ ደረጃና በሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤቶች እስከ 2005 ድረስ በሁሉም የትምህርት እርከኖች እስከ 2015 ድረስ ለመፍታ አቅዳለች

(https://www.indexmundi.com/ethiopia/millennium-development-goals.html)። ይህንን ዕቅድ በጥናት መዳሰስና ያለበትን ሁኔታ ማየትም ተገቢ ነው።

በዚህ ጥናት የተፈተሹ መማሪያ መጻህፍት በአዲስ መልክ በ2006ዓ.ም ተዘጋጅተው በ2007/8 ዓ.ም ስራ ላይ መዋላቸውና ከዚህ በፊት በጥናት የመፈተሽ እድል ያልነበራቸው መሆኑ መጻህፍቱን በተመለከተ አስተያየት ለመስጠት እድል የፈጠረ ነው። ጥናቱም በዋናነት ይህን ክፍተት ለመሙላት የተነሳ ነው። የስርዓተጾታ ጉዳይ በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ልዩ ትኩረት (cross cutting issue) ተሰጥቶት የባህል ለውጥ ለማምጣት እየተሰራ ነው። ይህ ጥናትም መጻህፍቱ ያሉበትን ሁኔታ ለማሳየትና ተጨማሪ ጥናቶችን ለሚያካሂዱም መነሻ ሃሳብ ለመስጠት ሊጠቅም ይችላል።

ይህ ጥናት የሶስተኛና አራተኛ ክፍልን ለማስተማር በስራ ላይ ባሉት የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ላይ ብቻ ያተኮረ ነው። በዚህም በአጠቃላይ በምንባቦችና በልዩልዩ መልመጃዎች የስርዓተጾታ ጉዳይ፣ አቀራረቡ ተፈትሿል። ጥናቱ ከዚህ ውጭ ባሉ የክፍል ደረጃዎች ላይ አላተኮረም። ሌሎች የትምህርቱ ይዘቶችንም አልተመለከተም። በጥናቱ ወንዶችና ሴቶች የሚሳተፉባቸውን ማህበራዊ ሚናዎች፣ የወንድና ሴት ገጸባህሪ መጠንና ውክልና ተፈትሸዋል።

የጥናቱ ዓብይ ዓላማ የሶስተኛና የአራተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ከስርዓተጾታ ፍትሃዊነት አንጻር ምን እንደሚመስሉ መመርመር ነው። በዚህ መነሻነትም በጥናቱ የሚከተሉትን መሰረታዊ ጥያቄዎች ለመመለስ ተሞክሯል። ጥያቄዎቹም፡- በመማሪያ መጻህፍቱ ሴቶችና ወንዶች በስም የቀረቡበት ድግግሞሽ ምን ያህል ነው? በመማሪያ መጻህፍቱ የሴት- ወንድ የስም ጥምርታ (ሬሾ) ምን ያህል ነው? በመማሪያ መጻህፍቱ ሴቶችና ወንዶች የቀረቡባቸው ዋናዋና ሚናዎች ምን ምን ናቸው? እና ሴቶችና ወንዶች የተወከሉባቸው ዋናዋና ነገሮች ምንምን ናቸው? የሚሉት ናቸው።

## የአጠናን ዘዴ

ይህ ጥናት ገላጭ የጥናት ንድፍን የተከተለ ነው። በተሰበሰበውና በተተነተነው የመረጃ አይነት አንጻርም መጠናዊና አይነታዊ አቀራረብን በማጣመር ተጠቅሟል።

በተጠኝነት የተገለጹት በአሁኑ ስዓት (2007/8ዓ.ም ጀምሮ) ስራ ላይ ያሉት የሶስተኛና የአራተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ናቸው። ሁለቱ የክፍል ደረጃዎች የተመረጡበት ምክንያት መጻህፍቱ ከአንደኛና ከሁለተኛ ክፍሎች ሰፋ ያሉ ተግባራትና ምንባቦች ያሏቸው በመሆኑ ከጥናቱ ዓላማ አንጻር በቂ መረጃ በመሰብሰብ ለህጻናት ስብዕና የተሰጠውን ትኩረት ለመመርመር ያስችላሉ ተብሎ በመታመኑ ነው። በመማሪያ መጻህፍቱ ያሉ አጠቃላይ ምንባቦችና ተግባራት/መልመጃዎች በሙሉ ተፈትሸዋል። ተጠኝዎችን ለመምረጥ ዓላማተኮር የንሞና ስልት ጥቅም ላይ ውሏል።

ይህ ጥናት የሰነድ ፍተሻ ጥናት በመሆኑ የመረጃ መሰብሰቢያ ስልቱም የሰነድ ፍተሻ ስልት ነው፡፡ ለዚህም ለየዓላማዎቹ መረጃዎችን ለመሰብሰብ የሚያስችሉ ቼክሊስቶች ጥቅም ላይ ውለዋል። ቼክሊስቶቹም የጥናቱ ዓላማዎች የሚፈልጉትን መረጃ ለመሰብሰብ ማስቻላቸው በአጥኝው ሁለት የስራ ባልደረቦች (ሁለተኛ ዲግሪ ያላቸውና ከ10 ዓመት በላይ በሁለተኛ ደረጃና በኮሌጅ ያስተማሩ) አስተያየት ተሰጥቶባቸው ተከልሰው ጥቅም ላይ ውለዋል። መረጃዎችን በመሰብሰብ ሂደትም ግንዛቤ የተፈጠረላቸው ተመራቂ የኮሌጅ ተማሪዎች ተሳትፈውበታል። ከእያንዳንዱ መጽሃፍ መረጃ ከተሰበሰበ በኋላ መረጃው በሁለተኛ መረጃ ሰብሳቢ ትክክለኛነቱ እንዲረጋገጥ ተደርጓል። በአጥኝውም በድጋሜ ተረጋግጧል። አሰባሰቡም ተፈላጊ መረጃዎችን ከነገጻቸው በተዘጋጀው ቼክሊስት ላይ ማስፈር ነበር። ከሰነድ የተገኙ መረጃዎች ከተደራጁ በኋላ በካይ ካሬ፣ በድግግሞሽ ቆጠራ፣ በመቶኛ፣ በሬሾ እንዲሁም አይነታዊ በሆነ መልክ በማብራራት ተተንትነዋል።

የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርትቢሮ (2002፣115) እንደሚገልጸው ‹‹የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የመማሪያ መጻህፍቱን በየጊዜው እየገመገሙ ለሚመለከተው አካል የመላክ ሃላፊነት አለባቸው።›› አጥኝው በሙያው ያለፈና አሁንም በክረምቱ መርሃ ግብር መምህራንን የማስተማር ስራ እየሰራ ይገኛል። ይህን መሰረት በማድረግም የሶስተኛና የአራተኛ ክፍል መማሪያ መጻህፍትን ለመገምገም ተሞክሯል።

## የውጤት ትንተናና ማብራሪያ

የጥናቱ ዓብይ ዓላማ የሶስተኛና የአራተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍት የስርዓተጾታ ፍትሃዊነት አንጻር

ምን እንደሚመስሉ መመርመር ነው። ይህን ዓላማ ዳር ለማድረስ የተሰበሰቡ መረጃዎችም ከመሰረታዊ ጥያቄዎቹ አንጻር ቀጥለው ቀርበዋል።

የጥናቱ የመጀመሪያ መሰረታዊ ጥያቄ በመማሪያ መጻህፍቱ ሴቶችና ወንዶች በስም የቀረቡበት ድግግሞሽ ምን ያህል ነው? የሚል ነው። ይህን የተመለከተው መረጃም ቀጥሎ በድግግሞሽ ቆጠራ፣ በድምር፣ በመቶኛና በካይ ካሬ ተሰልቶ ቀርቧል።

ሴቶችና ወንዶች በስም በድግግሞሽ ቆጠራ፣ በድምር፣ በመቶኛና በካይ ካሬ ስሌት

| የክፍል ደረጃ | የጾታ ድግግሞሽ | | Value<br>ብዛት | Df<br>የነጻነት ደረጃ | Sign<br>የጉልህነት ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ወንድ | ሴት | | | |
| 3ኛ | 36 | 51 | 2.00 | 1 | .157 |
| 4ኛ | 20 | 15 | | | |
| ድምር | 56(45.9%) | 66(54.09%) | | | |

*(በካይ ካሬ ትንተና ጊዜ ሴት=1 እና ወንድ=2 ውክልና ተሰጥቶ ነበር፡፡)

ከላይ ከቀረበው ሰንጠረዥ እንደተመለከተው በድግግሞሽ ቆጠራና በመቶኛ ተሰልቶ በሶስተኛና በአራተኛ ክፍሎች ወንዶች 56 ጊዜ (45.9%)፣ ሴቶች 66 ጊዜ (54.09%) የተደጋገሙ ሆኖ ተገኝቷል። የካይ ካሬ ፍተሻ እንዳሳየውም $p>0.05$ ሆኗል፡፡ የጉልህነት ውጤቱም .157 ሆኗል። ይህም በሁለቱ ጾታዎች መካከል የጎላ ልዩነት እንደሌለ የሚያሳይ ነው። ከተገኘው መረጃ መረዳት የሚቻለው አንጻራዊ በሆነ መልክ የስርዓተጾታ ፍትሃዊነቱ በጥሩ ሁኔታ ላይ እንዳለ ነው። ይህ ውጤት በሆንግ ኮንግ የJackie (2002) የጥናት ውጤት ጋር ተመሳሳይ ሆኗል። አጥኝው በመማሪያ መጻህፍቱ ለጾታ ፍትሃዊነት ትኩረት መሰጠቱን ጠቁመዋል።

የጥናቱ ሁለተኛ መሰረታዊ ጥያቄ በመማሪያ መጻህፍቱ የሴት- ወንድ የስም ድግግሞሽ ጥምርታ (ሬሾ) ምን ያህል ነው? የሚል ነው። የተገኘው ውጤት እንዳመለከተውም ወንዶች 56 ጊዜ፣ ሴቶች 66 ጊዜ በስም በመደጋገም መጥተዋል። ሴቶች ለወንዶች ሲካፈል 1.12 ለ1 ነው። ይህ ሬሾም በሁለቱ ጾታዎች መካከል የጎላ ልዩነት ስለሌለ የስርዓተጾታ ፍትሃዊነቱን የተሻለ ያደርገዋል። ይህ ምጥጥን ኢትዮጵያ በ2005 በሚሊኒየም እድገት ዕቅድ እደርስበታለሁ ካለችው የጾታ እኩልነት ግብ አንጻር የተሻለ መሆኑን የሚያሳይ ነው።

የጥናቱ ሶስተኛ መሰረታዊ ጥያቄ ደግሞ፣ በመማሪያ መጻህፍቱ ሴቶችና ወንዶች የቀረቡባቸው ዋናዋና ሚናዎች ምን ምን ናቸው? የሚል ነው። ከተገኘው መረጃ ለማየት እንደሚቻለው ሴቶችና ወንዶች በየግላቸው ሲያከናውኗቸው የተስተዋሉ ሚናዎች አሉ። በሁለቱም የክፍል ደረጃዎች የቀረቡት ሚናዎችም የሴቶች 36 (42.9%) ሲሆኑ የወንዶች ደግሞ 48 (57.1%) ናቸው። የሴቶች ሚና ሲታይ ዋናዋና በሚባል መልኩ ብዙዎች የተሳተፉበት ከፍተኛ ድግግሞሽ ያለው ሚና የለም። ለምሳሌ ያህል የተስተዋሉ የሴቶች ሚና፣ ሴቶችን መገረዝ፣ ዳቦ መግዛት፣ ዳቦ መሸጥ፣ ገንዘብ መቀበል፣ ልጅ ማስከተብ፣ ተማሪ መሆን፣ የህክምና ምክር ሰጭ መሆን፣ በሽተኛ መንከባከብ፣ መብት መጠየቅ፣ የመጀመሪያ እርዳታ ሰጭና ሩጫ ሰልጣኝ መሆን ተስተውለዋል።

የወንዶች ሚና ሲታይ በመጠኑም ቢሆን ድግግሞሹ ከሴቶቹ ሻል ያለ ነው። ዋና ዋና በሚባል መልኩ ብዙ ወንዶች የተከሰቱባቸው ሚናዎች በእግር መጓዝ (እግረኛ)፣ ኳስ ተጫዋች፣ በሽተኛ ተሽካሚ መሆን፣ ሩጫ ደጋፊ መሆን፣ ሳር ቤት መክደን፣ ፖሊስና ሹፌር ሆኖ መስራት ናቸው። እነዚህ ሚናዎች አንጻራዊ በሆነ መልኩ ብዙ ወንዶች የተሳተፉባቸው ናቸው።

ከዚህ አንጻር የስርዓተጾታ ሲታይ ፍትሃዊነቱ ለወንዶች ያደላ ነው ማለት ነው። ምክንያቱም ብዙ ድግግሞሽ ያላቸው ሚናዎች የቀረቡት ለወንዶች ሆኖ ተስተውሏል።

ወንዶችና ሴቶች በጋራ የተሳተፉባቸው ዋናዋና (ብዙዎቹ የተሳተፉባቸው) ሚናዎችን በተመለከተ፣ ከተገኘው መረጃ ለማየት እንደሚቻለው ወንዶችም ሴቶችም በጋራ የተሳተፉባቸው 49 (58%) ሚናዎች ናቸው። ይህም ከላይ በተናጠል ከቀረቡት ሚናዎች ጋር ተደምሮ 84 ሚናዎች በመጻህፍቱ ቀርበዋል። ከ84ቱም 49(58%)ቱ አብዛኛዎቹን በጋራ እንዲያከናውኗቸው ሆኖ መቅረቡ ለእኩልነት ከተሰጠው ትኩረት አንጻር ጥሩ ነው። ከጋራ ሚናዎች መካከል ሼፍ፣ ትራፊክ፣ መሃንዲስ፣ አርሷደር፣ ንብኝ፣ ሽክላ መስራት፣ አረም ማረም፣ ችግኝ መትከል፣ ይጠቀሳሉ። ሁለቱም ጾታዎች በብዛት ከተሳተፉባቸው ሚናዎች ዋናዋና የሆኑት (ብዙዎቹ ተሳተፉበት)፣ እርከን መስራት፣

በማህበራዊ ጉዳዮች መወያየት፣ አካባቢ ማጽዳት፣ ተረት ማዳመጥ፣ አርሶአደር መሆን፣ ስብሰባ መሰብሰብ፣ የሃኪም ምክር መቀበል፣ የእድር አባል መሆን የሚሉት በጣም በርካታ ወንዶችም ሴቶችም የተሳተፉባቸው ሚናዎች ናቸው።

ይህ ውጤት Akam (2009) የማርክሲስት አንስታይ ንድፈሃሳብ አቀንቃኞችን ጠቅሰው ሴቶች በተለያዩ ማህበረሰቦች ውስጥ አነስተኛ ክፍያ ባላቸው ስራዎች ይሳተፋሉ ከሚሉት የራቀ አይደለም፡፡ የወንዶች ሚና ሲታይ፣ በመኪና መንገድ እግረኛ መሆን፣ ኳስ ተጫዋቾች፣ በሽተኛ ተሸካሚ መሆን፣ ሩጫ ደጋፊ መሆን፣ሳር ቤት መክደን፣ፖሊስና ሹፌር ሆኖ መስራት ዋናዋናዎቹ ናቸው። ከዚህ አንጻር ቋንቋው የወንዶችን ሚና አጉልቶ የማሳየት ሁኔታ ተስተውሎበታል፡፡ ውጤቱ Taylor (2003) በጥናታቸው  መማሪያ መጻህፍቱ ትንሽ ወንዶችን የሚያሞግሱ፣ ሴቶችን የሚያኮስሱ ነበሩ ካሉት ጋር የሚቀራረብ ነው። ውጤቱ Akam (2009)ና Toci & Aliu (2013) እንደሚያስረዱት ይህ ውጤት ወላጆችም ሴት ልጆቻቸው እንዲሰሩ የሚመኙትን የገደበ ነው። ፖሊስ፣ ሹፌር፣ ኳስ መጫወት ሁልጊዜ የወንዶች እንደሆኑ እንዲገምቱ እድል የሚፈጥር ነው ከሚሉት ሃሳብ ጋርም ተቀራራቢ ነው።

በአጠቃላይ ከዚሁ ዓላማ አንጻር ወንዶችና ሴቶች በጋራ የቀረቡባቸውን ሚናዎች ከጠቅላላው 84 ሚናዎች መካከል 49ኙን በእኩል ሁኔታ የተሳተፉ በመሆናቸው ፍትሃዊነቱ ጥሩ ነው።

የጥናቱ የመጨረሻ መሰረታዊ ጥያቄ ሴቶችና ወንዶች የተወከሉባቸው ዋናዋና ነገሮች ምንምን ናቸው? የሚል ነው። ይህን በተመለከተ ከተገኘው መረጃ ለማስተዋል እንደተቻለው ሴቶች የተወከሉባቸውና ወንዶች የተወከሉባቸው ጉዳዮች ሲታዩ ልዩነት አላቸው። መሰረታዊ ልዩነቱም ወንዶች በአንጻራዊነት በማኅበረሰቡ የተሻሉትን ውክልናዎች መያዛቸው ነው። ለምሳሌ- ዶክተር፣ የባንክ ባለሙያ፣ ሞዴል መምህር፣ በስራ ክፍፍል ማመን፣ የሚሉት በአመዛኙ የበላይነት የሚታይባቸው ናቸው። እነዚህም ሴቶቹ ያልተወከሉባቸው ማህበራዊ ውክልናዎች ናቸው። ወንዶች፣ የበላይነት፣ ቁጡነት፣ አጥቂነት፣ መፍትሄ ሰጭነት፣ መጣላት፣ ወፍራም፣ ዛፍ፣ ሰሌዳ፣ የፈላውሃ፣ ወረርሽኝ፣ መሬት፣ ጥቁር፣ ረባሽ በሚሉ አይነት ውክልናዎችም ቀርበዋል። በአንጻሩ ሴቶች የተወከሉባቸው ሲታዩ ታታሪነት፣ ደስተኛነት፣ መዝናናት፣ ንብ፣ ፈጣን፣ የቀይዳማ፣ ጠይም፣ መልከኛ፣ የሚሉትን የተሻሉ ውክልናዎች ይዘዋል። በተቃራኒም አጭር፣ ጭልፊት፣ ጫጩት፣ አህያ፣ በውሻ መነከስ የሚሉት ዝቅ ያለ ደረጃ ያላቸው የሴቶች ማህበራዊ ውክልናዎች ናቸው። ሁለቱም ጾታዎች የተወከሉባቸው በሽተኛ፣ ዓይነስውር፣ ረጅም፣ መታረቅ፣ ጎበዝ፣ ገበሬ፣ ፈጣን የሚሉት ናቸው። ነገር ግን በሁለቱም ጾታዎች ሴት ሲባል ትዝ በሚል መልክ፣ ወይም ወንድ ሲባል ትዝ በሚል መንገድ የተስተዋሉ ተደጋጋሚ ወይም ብዙ ሴቶች ወይም ወንዶች የቀረቡባቸው ውክልናዎች የሉም። ምናልባት በሁለቱም ጾታዎች በተደጋጋሚ በመከሰቱ ‹‹ገበሬ›› ሲባል ወንድም ሴትም ትዝ ሊል ይችላል። ይህ ውጤት Candida & et al(1999)፣ ሴቶች ተደጋፊ  ወንዶች ደግሞ  ራሳቸውን የቻሉ፣ ጎበዝ፣ ምክንያታዊ፣ ሰጭ፣ ሆነው ብዙ ጊዜ ይገለጻሉ ከሚሉት ጋር ተደጋጋፊ ነው።

### መደምደሚያና አስተያየት

#### መደምደሚያ

የጥናቱ የመጀመሪያ ዓላማ በመማሪያ መጻህፍቱ ሴቶችና ወንዶች በስም የቀረቡበት ድግግሞሽ ምን ያህል እንደሆነ መለየት የሚል ነው። ከዚህ ዓላማ አንጻር በሶስተኛና በአራተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ ሴቶች 66 ጊዜ፣ ወንዶች ደግሞ በአማካይ 56 ጊዜ ተከስተዋል። የካይ ካሬ ፍተሻ እንዳሳየውም $p>0.05$ ሆኗል። የጉልህነት ውጤቱም .157 ሆኗል። ይህም በሁለቱ ጾታዎች መካከል የጎላ ልዩነት እንደሌለ የሚያሳይ ነው። ከዚህ አንጻርም የስርዓተጾታ  ፍትሃዊነትም አለው ማለት ይቻላል። ይህ የሴቶች መጠነኛ ብልጫ አለ ማለት ግን በማህበራዊ ሚናዎቻቸውም ጉልህ የሆነውን ድርሻ ወስደዋል ማለት አይደለም።

የጥናቱ ሁለተኛ ዓላማ በመማሪያ መጻህፍቱ የሴት- ወንድ ጥምርታ (ሬሾ) ምን ያህል እንደሆነ መመርመር የሚል ነው። ከዚህ ዓላማ አንጻር በሶስተኛና በአራተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ የሴቶችና የወንዶች ጥምርታ 1.12፡1 ነው። ወይም 1.12 ሴት ለ1ወንድ ነው። ይህም በመካከላቸው ያለው ልዩነት ዝቅተኛ እንደሆነ መረዳት ይቻላል። የስርዓተጾታ ፍትሃዊነቱም የተሻለ ነው ማለት ይቻላል።

የጥናቱ ሶስተኛ ዓላማ ደግሞ፣ በመማሪያ መጽሃፎቹ ሴቶችና ወንዶች የቀረቡባቸው ዋናዋና ሚናዎች ምን ምን እንደሆኑ መመርመር የሚል ነው። ከዚህ ዓላማ አንጻር መማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ ሴቶች ብቻቸውን የጎላና በተደጋጋሚ የተከሰቱበት ሚና የላቸውም። ከመረጃው የተስተዋለው ሴቶች በአንድ ሚና ላይ አንዴ ታይቶ መጥፋት ነው። ወንዶች ሲታዩ ደግሞ፣ በመኪና መንገድ እግረኛ መሆን፣ ኳስ ተጫዋቾች መሆን፣ በሽተኛ ተሸካሚ መሆን፣ ሩጫ ደጋፊ መሆን፣ ሳር ቤት መክደን፣ ፖሊስና ሹፌር ሆኖ መስራት በሚሉት ዋናዋና ሚናዎች የተሳተፉ ናቸው።

ከዚህ መረጃ ለመረዳት የሚቻለው በአንድ ሚና በሰፊው ተሳታፊ ሆነው የተስተዋሉት ወንዶች መሆናቸውን ነው። ከዚህ ዓላማ አንጻር የወንዶች የበላይነት ተስተውሏል ማለት ይቻላል፡፡ በዚህ የተናጠል ሚና የስርዓተጾታ አድሎ መኖሩን መረዳት ይቻላል።

የጥኛቱ የመጨረሻ ዓላማ ሴቶችና ወንዶች የተወከሉባቸው ዋናዋና ነገሮች ምንምን እንደሆኑ መፈተሽ የሚል ነው። ከዚህ ዓላማ አንጻር በሶስተኛና በአራተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ የተገኘው መረጃ እንደሚያሳየው፣ ሴት ሲባል ወይም ወንድ ሲባል ትዝ በሚል መንገድ የተስተዋሉ ውክልናዎች የሉም ማለት ይቻላል። ብዙ ሳይደጋገሙ የቀረቡ ውክልናዎች ሲታዩ ግን ሴቶች የተወከሉባቸው ነገሮች አንጻራዊ በሆነ መልክ ከወንዶች ያነሱ ናቸው ማለት ይቻላል። ከዚህ አንጻር ደግሞ የስርዓተጾታ ፍትሃዊነት ክፍተት አለ ማለት ይቻላል።

## አስተያየት

የጥናቱ ዓብይ ዓላማ የሶስተኛና የአራተኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጻህፍት የስርዓተጾታ ፍትሃዊነት ምን እንደሚመስሉ መመርመር ነበር። በዚህ መነሻነትም የተለያዩ መረጃዎች ተሰብስበው ተተንትነዋል፤ መደምደሚያ ላይም ተደርሶባቸዋል። ከድምዳሜው በመነሳትም አጥኚው የሚከተሉትን አስተያየቶች ለመጠቆም ሞክሯል።

- ወደፊት የስርዓተ-ትምህርት አዘጋጆች በሚያዘጋጇቸው የመማሪያ መጻህፍት ውስጥ ወንዶችንና ሴቶችን እኩል አመጣጥኖ የማቅረብ ልምዳቸውን ከዚህ በላይ የስርዓተጾታ ፍትሃዊነቱን አጠናክረው ቢቀጥሉበት፣
- የስርዓተትምህርት አዘጋጆች በሚያዘጋጇቸው መጻህፍት ውስጥ የወንዶች ማህበራዊ ሚና፣ የሴቶች ማህበራዊ ሚና፣ የወንዶችና የሴቶች የጋራ ማህበራዊ ሚና በውል ተለይቶ ጎላ ባለ (ተደጋጋሚነት ባለው) መልኩ ቢቀርብ፣ ወይም ሁሉንም ሚናዎች ነካነካ ባደረገ መልክ ባይቀርብ፣
- የስርዓተ-ትምህርት አዘጋጆች ውክልናን በተመለከተም ሴት ሲባል ወይም ወንድ ሲባል ትዝ በሚል (ተደጋጋሚነት ባለው) መልክ፣ ፍትሃዊነትን በጠበቀ መልክ ለማቅረብ ጥረት ቢያደርጉ፣
- በመስኩ ጥናትና ምርምር የማድረግ ፍላጎት ያላቸው ባለድርሻ አካላትም በመማሪያ መጻህፍት ውስጥ ያለ የጾታ ፍትሃዊነት በህጻናት እድገት ላይ ያለው አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ተጽዕኖ ከፍተኛ በመሆኑ መጽሃፍቱን በተደጋጋሚ በማጥናት ለስርዓተ-ትምህርት አዘጋጆች በቂና አስተማማኝ መረጃ በመስጠት ቢሳተፉ መልካም ነው የሚሉት ናቸው።

## ዋቤዎች

የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት-ቢሮ። (2002)። *የስርዓተትምህርት ዝግጅትና ትግበራ ዋና የስራ ሂደት ተግባራት ማስፈጸሚያ ስትራተጂና ልዩልዩ መመሪያዎች*። የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት-ቢሮ፡ ባህርዳር።

Akam ,P. E. (2009). T*he Effect of Gender Division of Labour on the Education of Rural School Children. The case of two primary schools in Medig,Cameroon. Depart ment of Sociology and Human Geography*. (Master thesis). Universiteteti Oslo.

Candida, M. et al. (1999). *A Guide to Geneder- Analysis Frameworks*. UK: An Oxfam Publication.

Carole B.(2009). *Promoting Gender Equality through Textbooks: A methodological guide*. Published by the United Nations Educational, Scientific and Cultural Organization. France.

Cornwall, A., Harrison, E. & Whitehead, A. (2007). *Gender Myths and Feminist Fables: The struggle for interpretive power in gender and development.* England: Blackwell publishing.

Cranny-Francis, A. et al (2003). G*ender Studies Terms and Debates*. New York Basingstoke: Palgrave Macmillan. Palgrave Macmillan publisher.

Hornby,A.S. (1989). *Oxford Advanced Learner's Dictionary*. 4th Edition. UK: Oxford Univ Press. https://www. indexm undi.com/ethiopia/millennium-development-goals. html (16/ 9/2010)

Jackie,F.K.Lee.(2002). *Geneder represenetation in HongKong English Text Books*. Piter Collins: The University of New South Wales.

Kevane, M. (2004). Women and Development in Africa: How Gender Works. Boulder London: Lynne Rienner Publishers.

Taylor,F. (2003). Contenet analysis and Geneder Sterotypes in Children's Books.

American Sociological Association. *Teaching Sociology,* 31 (3), 300-311.

Toci, A & Aliu, M. (2013). Geneder stereotypes in current children's English books used in elemenetary schools in the republic of Macedonia. American International *Journal of Contemporary Research,* 3 (12), 32-38.

Wondifraw Dejene. (2017). Assessing Ethiopian Primary School Second Cycle Social Studies Textbooks for Adequate Reflections of Multiculturalism. Dire Dawa University, College of Social Science and Humanities, Department of Education. *Journal of Education and Practice,* 8(10), 117-126.